# ታላቅ የተቃውሞ    ሰላማዊ ሰልፍ ጥሪ
# ለኢትዮጵያውያንና ለወዳጆቻችን!!!




## በጀርመን/ፍራንክፈርት

የዘረኛና አምባገነኑ የወያኔ ቡድን በሰላማዊ ወገኖቻችን ላይ እያደረሰ ያለው ግፍና በደል ከመቸውም ጊዜ በላይ እየጨመረ በመምጣቱ ምክንያት በተለያዩ አህጉር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የተቃውሞ ሰልፍ በማድረግ ላይ መሆናቸው ይታወቃል ስለዚህ እኛም በጀርመን የምንገኝ ኢትዮጵያውያን የዚሁ ትግል አጋር በመሆን

1. በፈጠራ ወንጀል በቅርቡ የታሰሩት እስክንድር ነጋ,አንዱዓለም አራጌና ሌሎችም ላለፉት 20 ዓመታት በወያኔ አስር ቤት በግፍ የሚሰቃዩት የፖለቲካ እስረኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱና እኛም በጀርመን በስደት የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ህዝቡ ለመብቱ መከበር ለሚያደርገው ትግል ከጎኑ መሰለፋችንን ለማረጋገጥ.
2. በብዙ ሺህ ለሚቆጠሩ ወገኖቻችን መፈናቀል ምክንያት የሆነው በደቡብና በምዕራብ ኢትዮጵያ በኢንቨስትመንት ስም ህግ ወጥ በሆነ መንገድ የሚደርገውን የመሬት ችብቸባ በመቃወም
3. የዘረኛው ወያኔ ቡድን ሰለባ በመሆን በጀርመን ሀገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች መብታቸው እንዲከብርና ሌሎችም በርካታ ኢትዮጵያ ውስጥ እየተፈጸሙ ያሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን በስደት ለምንኖርበት ህዝብና መንግስት ለማሳወቅ አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅቶች ተጠናቁዋል. ስለዚህ በወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለው ግፍና በደል የሚሰማችሁ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ወግኖቻችን በሙሉ ከታች ከተገለጸው ቀንና ሰዓት ከስፍራው በመገኘት በጋራ ድምጻችንን እንድናሰማ ወገናዊ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን..

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !!
የሰልፉ አስተባባሪ ግብረሀይል

ቀን - 29.11.2011
መገናኛ ቦታ- Frankfurt Hauptwache (Kaufhof) ፊት ለፊት
ሰዓት- ከቀኑ 11:00 ሰዓት 11:00 Uhr
ሰልፉ ከ Hauptwach ተነስቶ በEschersheimerland str አድርጎ ወያኔ ኮንሱላንት ፊት ለፊት ይጠናቀቃል በቀጥታ ከስፍራው ለመድረስ በ U- bahn 1,2,3 በመያዝ Holzhausen str. በመወረድ በቀላሉ ያገኙታል
Eschersheimerland Str. 105-107

ማሳሰቢያ-- ከየትኛውም አካባቢ ለምትነሱ ወገኖቻችን የትራንስፖርት አገልግሎት ለማግኘት ከታች በተዘረዘሩት የስልክቁጥር በመደወል በቂ መረጃ የሚያገኙ መሆንዎን እየጠቆምን በያካባቢው ለአውቶቡስ ምደባ ይረዳን ዘንድ በቅድሚያ እንዲመዘገቡ ከታላቅ አክብሮት ጋር እናስታውቃለን..

017659945946 017671947758 017671056015 015251436914 017625998578 017671662780 017659947979 -017669348215 015225442512 017674121938. 017674105888 017673287381 01636379583 017671651797 015776203683